የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
አዲስ አበባ ሚያዝያ ፮ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 31
ADDIS ABABA 14th April 2011

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፮/፪ሺ፫

የተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ……………ገጽ ፭ሺ፯፻፺፰

## CONTENTS

Regulation No. 206/2011

Vehicles Identification, Inspection and Registration Fees Council of Ministers Regulation ………………Page 5798

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፮/፪ሺ፫

## የተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ ክፍያን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና በተሽከርካሪ መለያ፣ መመዝገቢያና መመርመሪያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፹፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፵፯(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል::

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፮/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪. ትርጓሜ**

በተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፹፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፪ የተሠጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል::

**፫. የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን በሚመዘገቡ ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል::

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 206/2011

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR VEHICLES IDENTIFICATION, INSPECTION AND REGISTRATION FEES

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 47(1) of the Vehicles Identification, Inspection and Registration Proclamation No. 681/2010.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Vehicles Identification, Inspection and Registration Fees Council of Ministers Regulation No. 206/2011".

**2. Definitions**

Definitions provided for under Article 2 of the Vehicles Identification, Inspection and Registration Proclamation No. 681/2010 shall be applicable to this Regulation.

**3. Scope of Application**

This Regulation shall be applicable with respect to vehicles to be registered by the Federal Transport Authority.

፬. <u>የአገልግሎት ክፍያዎች</u>

ለተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያ፣ መመዝገቢያና ተያያዥነት ላላቸው አገልግሎቶች የሚጠየቀው ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከተው መሠረት ይሆናል::

፭. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል::

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፮ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

4. **<u>Fees</u>**

Fees to be charged for identification, inspection and registration of vehicles and related services shall be as prescribed in the schedule attached hereto.

5. **<u>Effective Date</u>**

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 14th day of April, 2011.

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

## ሠንጠረዥ
## የአገልግሎት ክፍያዎች

| ተ.ቁ | | | የአገልግሎት ዓይነት | ክፍያ (ብር) | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | | የባለንብረት መታወቂያ ደብተር | | |
| | 1.1 | | ለሞተር ሳይክሎች | 8 | 00 |
| | 1.2 | | ለሌሎች ተሽከርካሪዎች | 15 | 00 |
| | 1.3 | | ዝርዝር ጉዳዮችን ለማስለወጥ በእያንዳንዱ ጉዳይ | 5 | 00 |
| | 1.4 | | በምትክነት ሲሰጥ ከዋና ክፍያ በተጨማሪ | 5 | 00 |
| 2 | | | የመለያ ቁጥር ሠሌዳ | | |
| | 2.1 | | የዕለት ሰሌዳ (ለአንድ ወር) | 250 | 00 |
| | 2.2 | | ቋሚ ሠሌዳ ለሞተር ሳይክል ሲሰጥ ወይም ሲተካ | 10 | 00 |
| | 2.3 | | ቋሚ ሠሌዳ ለሌሎች ተሽከርካሪዎች ሲሰጥ ወይም ሲተካ | 15 | 00 |
| | 2.4 | | ተላላፊ ሠሌዳ ሲሰጥ ወይም ሲታደስ (ለአንድ ዓመት) | 250 | 00 |
| 3 | | | ዓመታዊ የተሽከርካሪ ምርመራ የምስክር ወረቀትና የምዝገባ ተለጣፊ ምልክት | | |
| | 3.1 | | ለሞተር ሳይክል | 20 | 00 |
| | 3.2 | | ለግል አውቶሞቢሎችና የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የነጂውን መቀመጫ ጨምሮ:- | | |
| | | ሀ | ከአምስት የማይበልጥ መቀመጫ ላላቸው | 50 | 00 |
| | | | በተጨማሪ በመቀመጫ | 3 | 00 |
| | | ለ | ከ6 እስከ 44 መቀመጫ ላላቸው | 65 | 00 |
| | | | በተጨማሪ በመቀመጫ | 4 | 00 |
| | | ሐ | ከ45 እስከ 64 መቀመጫ ላላቸው | 70 | 00 |
| | | | በተጨማሪ በመቀመጫ | 4 | 00 |
| | | መ | 65 መቀመጫ ላላቸው | 80 | 00 |
| | | | በተጨማሪ በመቀመጫ | 4 | 00 |
| | 3.3 | | የጭነት ተሽከርካሪዎች | | |
| | | ሀ | ከ5 እስከ 70 ኩንታል ለሚጭኑ | 55 | 00 |
| | | | በተጨማሪ በኩንታል | 4 | 00 |
| | | ለ | ከ71 እስከ 120 ኩንታል ለሚጭኑ | 140 | 00 |
| | | | በተጨማሪ በኩንታል | 3 | 00 |
| | | ሐ | ከ120 ኩንታል በላይ ለሚጭኑ | 220 | 00 |
| | | | በተጨማሪ በኩንታል | 2 | 00 |
| | | መ | ማንኛውም ተሳቢ | 55 | 00 |
| | | | በተጨማሪ በኩንታል | 1 | 00 |
| | 3.4 | | ለልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ | 230 | 00 |
| | 3.5 | | ዝርዝር ጉዳዮችን ለማስለወጥ በእያንዳንዱ ጉዳይ | 4 | 00 |
| | 3.6 | | ለተለጣፊ የምርመራ ምልክት ግልባጭ | 8 | 00 |
| | 3.7 | | ለዓመታዊ የምዝገባ ካርድ ግልባጭ | 10 | 00 |
| 4 | | | መዝገብን፣ ሠነዶችንና መዘርዝሮችን ለማየት | | |
| | 4.1 | | መዝገብን፣ ሠነዶችንና መዘርዝሮችን ለመመልከት | 5 | 00 |
| | 4.2 | | በመዝገብ ወይም በሠነዶች ውስጥ የሚገኝ መረጃን ቅጅ ለመውሰድ በገጽ | 8 | 00 |
| | 4.3 | | የመዘርዝር ቅጅ ለመውሰድ በገጽ | 5 | 00 |

## SCHEDULE
## FEES

| No. | | | Type of Service | Fees (Birr) | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | | Title Certificate Book | | |
| | 1.1 | | for motor cycles | 8 | 00 |
| | 1.2 | | for other vehicles | 15 | 00 |
| | 1.3 | | for change of particulars, per item | 5 | 00 |
| | 1.4 | | for replacement, original amount plus | 5 | 00 |
| 2 | | | Identification Number Plates | | |
| | 2.1 | | for temporary identification number plates (for one month ) | 250 | 00 |
| | 2.2 | | for issuance or replacement of permanent identification number plates for motor cycles | 10 | 00 |
| | 2.3 | | for issuance or replacement of permanent identification number plates for other vehicles. | 15 | 00 |
| | 2.4 | | for issuance or renewal of transit plates (for one year) | 250 | 00 |
| 3 | | | Annual Vehicle Inspection Certificate and Registration Sticker | | |
| | 3.1 | | for motor cycles | 20 | 00 |
| | 3.2 | | for private motor cars and public service vehicles with capacity of, including driver's seat: | | |
| | | a | up to 5 seats | 50 | 00 |
| | | | plus per seat | 3 | 00 |
| | | b | from 6 up to 44 seats | 65 | 00 |
| | | | plus per seat | 4 | 00 |
| | | c | from 45 up to 64 seats | 70 | 00 |
| | | | plus per seat | 4 | 00 |
| | | d | 65 seats | 80 | 00 |
| | | | plus per seat | 4 | 00 |
| | 3.3 | | for trucks with load capacity of: | | |
| | | a | from 5 up to 70 quintals | 55 | 00 |
| | | | plus per quintal | 4 | 00 |
| | | b | from 71 up to 120 quintals | 140 | 00 |
| | | | plus per quintal | 3 | 00 |
| | | c | above 120 quintals | 220 | 00 |
| | | | plus per quintal | 2 | 00 |
| | | d | for any trailer | 55 | 00 |
| | | | plus per quintal | 1 | 00 |
| | 3.4 | | for special mobile equipment | 230 | 00 |
| | 3.5 | | for changes of particulars, per item | 4 | 00 |
| | 3.6 | | for duplicate of inspection certificate | 8 | 00 |
| | 3.7 | | for duplicate of annual registration card | 10 | 00 |
| 4 | | | Access to Registers, Records and Lists | | |
| | 4.1 | | for inspection of the registers, records or lists | 5 | 00 |
| | 4.2 | | for certified copy of a document contained in a register or record, per page | 8 | 00 |
| | 4.3 | | for copy of a list, per page | 5 | 00 |